# ከፓርላማ ቃሊቲ ደርሶ መልስ

በምትኩ አዲሱ

*መግቢያ*

*ማንም ዜጋ በጋራ ጉዳይ ላይ ሳይቆጠብ አሳቡን በጽሑፍና በንግግር መግለጽ መብትና ግዴታው ነው። ዝምታ እንደሆነ ለድህነትና ለሞት ይዳርጋል እንጂ ለአገር እድገትና ሰላም እምብዛም አይጠቅምም።*

*አንድ መንግሥት ደግሞ ክብሩና ብርታቱ ዜጋው ባለው ችሎታ ሁሉ እንዲሳተፍ ማመቻቸት ነው። ይኸ ሲሆን ማሕበረሰብ ይታደሳል፣ ያድጋል።*

*ተሃድሶ ደግሞ ወደ አለመረጋጋት የሚያመራ መሆን የለበትም፤ ጥንታዊነትን የሚሽር መሆን የለበትም። ከነበረው ውስጥ ጠቃሚውን መርጦ በዚያ ላይ ዘመንና ትውልድ በሚጠይቀው መሠረት ማነጽ ይኖርበታል።*

*እያንዳንዱ ትውልድ አዲስ ራእይ ይሻል። አዲስ ራእይ ያላቸው መሪዎችን ይፈልጋል። መሪዎች በሥልጣን ላይ "ዕድሜ ልክ" ሲቆዩ ጉዳቱ ለሁሉም ነው። እነዚህም እንደ ተገባቸው ማመን ይጀምራሉ፤ ሕዝቡን ለማሳመን ይጥራሉ። በሥልጣን መባለግ ይጀምራሉ። ይህ አባባል እውነትነቱ በኢትዮጵያ መሪዎች ብቻ አይወሰንም። መሪዎችን በሥርዓት መተካት የሚያስፈልገው እንግዲህ ለዚህ ነው።*

*በመጨረሻም፣ እነዚህን የመሰሉ ቁም ነገሮችን አንስቶ ለመወያየት ከአንድ ጎራ ውስጥ መገኘት አያሻም። የግድ የቅንጅት ወይም የሌላ አንጃ ደጋፊ መሆን አያሻም። ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻውን በቂ ነው። ፈርሃ እግዚአብሔርና ለሰው አክብሮት መኖሩ እጅግ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ እንደ አቅሙ የሚችለውን አስተዋጽዖ ማድረጉ ጠቃሚ ነው። ስሜታዊነትና የአሉባልታ ነፋስ በሚነፍስበት ሰዓት ደግሞ ጥቂት ዝግታ አይጎዳም፤ አይናቅም። አንባቢው ይህን ጽሑፍ በዚህ መንፈስ እንዲያነብበው ይጠየቃል።*

*የግንቦት ምርጫ*

*የግንቦት 97 ምርጫ ውጤት ያልተጠበቀ ነበር ብንል ግልጽ የሆነን ነገር መድገም ይሆንብናል። የምርጫው ውጤት ኢሕአዴግን አደናግጦ ያልተገባና ጸረ-ዴሞክራሲዊ እርምጃ እንዲወስድ አስገድዶታል። ቅንጅትንና ደጋፊዎቹን ደግሞ አስፈንድቆ ባልተሞከረና ባልተደራጀ ጉልበት በውጭ ድጋፍና ጠመንጃ የቆመን መንግሥት ለመጋተር አብቅቶታል። የኢሕአዴግ ችግሩ ከሚገባ በላይ በራሱ መታመኑ ነበር፤ እርቃኑን እንደ ሆነ አለመገንዘቡ ነበር። የቅንጅት ደግሞ ለምርጫው ሰሞን እንጂ ቀጥሎ ላለው ሁኔታ አለመዘጋጀቱና አቅሙን አለመመጠኑ ነበር።*

*ምን ማድረግ ይቻል ነበር ታዲያ? ለሚለው ጥያቄ ከግምታዊ መልስ አልፈን አጥጋቢ የሆነ ፍቺ ልንሰጥበት የምንችል አይመስለኝም። የሆነው ሆኗል፣ አይመለስም። ከንግዲህ ሊያሳስበን የሚገባው አሁን የሚታየው አዝማሚያና መጪው ነው።*

*ዶክተር ብርሃኑ እንዳስታወቀን ከሆነ ፓርላማ መግባትም ሆነ አለመግባት ሁለቱም በወቅቱ አስቸጋሪ ምርጫ ነበር። አንዱን መምረጥ አይቀርምና አለመግባቱ ተመረጠ። ውሳኔው የወህኒ*

መከራ ቢያመጣም ሊበታተን የደረሰን ሕዝባዊ ንቅናቄ እንዲጠናከርና ተምሞ ባሕር ማዶ እንዲሽጋገር አደርጎታል።

ኢሕአዴግን ደግሞ የራሱ ድርጊት ሳያጸጽተው እንዳልቀረ ከተከሰቱት ሁኔታዎችና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የደረሰበትን የውግዘት ጫና መጥቀስ ይቻላል። ዜጎችንና ጋዜጠኞችን ማሠሩና ማስፈራራቱ ሕዝቡን ይበልጥ እንዲጨክንና እንዲጠናከር አድርጎታል። ዴሞክራሲን ተግባራዊ እያደረግኩ ነው ብሎ በዓለም መንግሥታት ፊት የለፈፈውን ቃል መልሶ እየተጻረረ እንደ ሆነ አጋልጦበታል።

“ፓርላማ ግቡ”

አንድ ጉዳይ ግን መዘንጋት የለበትም። ይኸውም በአሜሪካን ኤምባሲ ሹማምትና አጋሮቻቸው ዛሬም እንኳ እንደ ጎን ውጋት ተደጋግሞ የሚሰማ፦ “ፓርላማ ግቡ፣ ሌላውን ሌላ ጊዜ በመወያየት ትፈቱታላችሁ” የሚለው ቃል ነበር። “ዴሞክራሲ እኮ ማሸነፍና መሸነፍ ሳይሆን ሂደት ነው … ፓርላማ ግቡ፣ የተመረጣችሁለትን ወንበር ያዙ” የሚለው ማለሳለሻ ነበር።

በዚያው ሰሞን በውጭ ዜና አውታሮች “ኢትዮጵያውያን ግትሮች ናቸው” ተባለልን። ፍትሕን ያሰባትም የለም። በአዲስ አበባ የሚልከሰከሱ ውሾች እንዳይገደሉ የተጯጯኸው የውጭ አገር ቆንስላና ዜጋ 197 ኢትዮጵያዊ በአደባባይ ሲደፋና ሺሁ ሲጋዝ ድምጽ አለማሰማቱ ለኛ ያለውን ግምት አስረጂ ነው። አሁን የሚገዛው መንግሥት ልብ ቢኖረው ነግ በኔ ባለ። ዛሬ የደገፈው የመሰለው ባዕድ ነግ እንደሚገለበጥበት ባወቀ። ከወገኑ ጋር ባዕዳንን ጣልቃ ሳያስገባ ወድቆ ተነስቶ ስምምነት ለመፍጠር በተጋ።

“ግትር” መባል ያልፈለገ እንግዲህ የተነገረውን እንዳ-ለ መቀበል ይኖርበት ነበር ማለት ነው። እነ ክቡር ዶክተር በየነ ጴጥሮስ ኤምባሲ ድረስ እየቀረቡ ስለ ምርጫው ውጤት ሆነ ሊወስዱት ስላላቸው እርምጃ መወያየት ቀጠሉ። ብዙም አልቆየ እነኝሁ ፓርላማ ለመግባትና ዴሞክራሲያዊ ፍልሚያ ለማፋፋም ተስማሙ። የተቀሩቱ ወደ ከርሸሌ በረሩ፤ ሃያ አንድ ወር ቆጠሩ።

እነ በየነ ጴጥሮስ ተሳሳቱ ይሆን? ምንስ ውጤት አስገኙ? ይህንንም አስረግጦ መናገር የሚቻል አይመስለኝም። ውጤቱ ምናልባት ውሎ ሲያድር ግልጽ መሆኑ ስለማይቀር ለጊዜው ዝምታ ይሻል ይሆናል። መሪዎቹ የወሰዱት እርምጃ ግን የጅምላ አስተሳሰብ መቅረቱን እያበሰረን ነው። ዴሞክራሲ አለመስማማትንም ይጨምራል፤ አቅጣጫና ዓላማን ቀይሮ ከባላጋራ ጋር ሳይቀር መነጋገር፣ ማደምና የራስን ጥቅምና መብት ማስከበርን ይጠይቃል። በዚህ ስልት መሠረት ውስልትና አይካሄድም ማለት አይደለም፤ የጥንቱ የጅምላ ፖለቲካ ሥፍራ እየጠበበው መጥቷል ማለት እንጂ።

ለማንኛውም ቅንጅት ለሁለት ተከፈለ። የታሰሩት መስከረም ወር ላይ ቢለቀቁም እነዚህንስ እንዴት ፓርላማ እንዲገቡ ማድረግ ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ገና አልተረሳም ነበር። ኢሕአዴግ መድረኩን እንዲጋራና የተረፈውን ቅንጅት እንዲያስተናግድ መገፋፋት አንዱ መንገድ ነበር።

የአሜሪካን ኤምባሲ ሹማምት ዛሬ ተቀያይረዋል። እመት ብራዚልና እመት ሀድልስተን ወደ ጡረታቸው ሄደው በነርሱ ፈንታ ጎረምሳው ያማ ሞቶ ተተክተዋል። ያማ ሞቶም የቀደሟቸው እመቶችና የበላያቸው የሆኑት እመት ፍሬ ዘር ከተናገሩት አንዳች ቃል ሳያዛንፉ “ፓርላማ ግቡ” ማለቱን ተያያዙት።

## አሳሪና ታሳሪ

የእስረኞቹን መፈታት በማቀናበርና ጨና በመፍጠር ረገድ ያማ ሞቶ ሚና ተጫውተዋል ማለት ይቻላል። ችግሩ አሁንም ኢሕአዴግን ድንጋጤው አልለቀቀውም። እስረኞቹ ሲፈትቱ ምን ይፈጠር ይሆን ማለት ያ-ለ ነገር ነውና። ታዲያ ኢሕአዴግ እንዳይጠየቅና የልቡን እንዲፈጽም ዋነኛ ብልሃቱ አራት መልክ ነበረው። አንዱ፣ የኤርትራን ጉዳይ እንደ እሳት ማዳፈኛ መጠቀም ነበር። የኤርትራን ጉዳይ ለኤርትራዊያን መተው ሲ-ገ-ባ እንዲያውም በአደባባይ “ኤርትራን የሚነካ ዐይናችንን ይነካል” እስከ ማለት ደርሷል። እርግጥ ከልብ ላይሆን ይችላል። እንዳይሰክን እንዳይገነፍል ማድረግ የተዋጣለት የፖለቲካ ቅመም ከሆነ ሰንብቷልና። ሁለተኛው፣ አልሆን ካለ ጥለንላችሁ የራሳችንን ድንበር እንከልላለን፤ ስትተረማመሱ ትኖሯታላችሁ የሚል ወሬ ማናፈስ ሲሆን፤ ሌላኛው፣ “አክራሪ አማራ” የምትል መንጠቆ መጠቀም ነበር። አራተኛውና ምናልባትም ለሰዓቱ ዓይነተኛ መድኃኒት ሆኖ የተገኘው “ሽብር ፈጣሪን መከላከል” የምትለዋ ዘይቤ ነች።

ሌላው ቁም ነገር የኤምባሲ ሹማምት ቢቀያየሩም ጉዳዩ እስካሁን እልባት አለማግኘቱ ነው። ውጤት ለማስመዝገብ “ፓርላማ ግቡ” የምትለዋን ትዛዝመሳይ ማስፈጸም ይገባልና። እንግዲያስ የተፈቱት የቅንጅት መሪዎች ፓርላማ መግባት ክብሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን በቅድሚያ ለነዚሁ ሹማምት መመሰጋገኛ ነው።

“አክራሪ አማራ” ደግሞ የክቡር ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውልንና የደጋፊዎቻቸውን አቋም ይመለከታል። እነዚህም “ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ነች፤ እናስመልሳለን” ይላሉ ተብሎላቸዋል። ይህንንም ብለው ከሆነ ይህን ቃል ያሰሙት መቼ እንደሆነና ዛሬም ይኸ አቋማቸው እንደሆነ ማስረገጥ ያሻል። በሌላ አነጋገር እነ ኃይሉ ሻውል እጅጉን ብሔረተኛነት (ኢትዮጵያዊነት) ተሰምቷቸዋል ነው። ይህ ደግሞ “አክራሪነት” ስለሚሆን ከእንደዚህ ዓይነቱ ጋር መደራደር አይቻልም። በአገር ጉዳይ ላይ ለመወያየት የሻ “አክራሪ” እንዳይባል የአገር ፍቅሩን ቀነስ ማድረግ ይጠበቅበታል እየተባልን እንደሆነ እንገንዘብ።

ቀስ በቀስ…

እርግጥ የተከበሩ ኢንጂኔርና አጋሮቻቸው ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ አገላለጻቸው ለአገሪቱ ኅልውና ከነርሱ የተሻለ የሚቀረቀር እንደሌለ መስሎ ይሆናል። ሌላው ሁሉ እንግዳና መጤ እንጂ ታሪካዊ ባለቤትነት ለእነርሱ እንደተገባቸው አስመስለው ይሆናል። ለነገሩ ከወደ ትግራይ የመጡትም የወቅቱ መሪዎች አስተሳሰባቸው ከዚህ አይለይም። የኢንጂኔሩ ግን በአብዛኛው የአገላለጽ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። አንዳንዶች “ኢትዮጵያ” መባልን እንደ ለምጽ ሲጠየፉት አላስችል ቢላቸው ያስወነጅላል?

ዞሮ ዞሮ የኢትዮጵያን ሉዑላዊ ክብር የሚንቁ ግድግዳ በሌለው ቤት ውስጥ ሆነው ገበናቸው የማይታይ የሚመስላቸው ብቻ ናቸው።

“አክራሪ ብሔረተኛ” በምትለዋ ቅመራ መሠረት እንግዲህ እነ ኃይሉ ሻውልን ማግለልና “ለዘብተኞቹን” የእስር ጓዶቻቸውን መነጣጠል ይቻላል ማለት ነው። ስልታቸው እንደ ውጋት ቶሎ አይለቅም ያልነው ከዚህ የተነሳ ነው። እንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን ሲቦረቡር አይታይም፤ ሲገነደስ እንጂ።

የቅንጅት መሪዎች ቃሊቲ ከመውረዳቸው በፊት ብዙ ጉዳይ ተድበስብሶ ነበር። አሁን ግን ብዙ ነገር አደባባይ እየወጣ ነው። ሃያ ስድስት ሰው ብቻ ሞተ የተባለው 197 ሆኖ ተገኝቷል። አጣሪ ኮሚቴ አጥንቶ ሪፖርት እንዳቀረበልኝ ሕጋዊ እርምጃ እወስዳለሁ ያለው መንግሥት እንደ ለመደበት ቃሉን ሲያጥፍ ታይቷል። አጣርተው ሪፖርት ያቀረቡትም ዛሬ ስደተኛ ሆነዋል። የተወሰደ እርምጃ የለም። ሊወሰድም አይችልም። ምክንያቱም አጥፊው ራሱን መልሶ ማረም አይቻለውምና ነው። ሌላ እንዳያርመው ደግሞ በምን ሥልጣን? በምን ሕግ? የታወጀልን “አብዮታዊ ዴሞክራሲ” እንግዲህ ይኸን ይመስላል። “አብዮት” ብቻ እንዳይባል ከመጽዋቹ ምዕራብ ጋር ሊያነካክስ ነው፤ “ዴሞክራሲ” ደግሞ ከጎሠኛነት ጋር የማይታረቅ ሆነ። “አብዮታዊ ዴሞክራሲ” የሰላ ማደናገሪያ መሆኑ ነው። የገነባውን ያፈርሳል፤ አብዮታዊ እንጂ ዴሞክራሲያዊ አይደለምና። ወደፊት ደግሞ ይኸው “አብዮታዊ ዴሞክራሲ” በ“ሕብረሰባዊ ዴሞክራሲ” እንዳይተካና ዘመናችንን እንዳያባክን እንስጋ።

መፍትሔው ቀላል ነው

ካሰብንበት የሚታየው ትርምስ መፍትሔው ቀላል ነው። መፍትሔው መያያዝ ነው። ሁሉም እንዲያያዝ ማድረግ አይቻል ይሆናል። ሆኖም ሌሎችም እንዳስተዋሉት በተቻለ መጠን ለጊዜያዊ ጥቅም አለመበገርና አለመንበርከክ ነው። ትልቁንና የጋራን ጥቅም ከሩቁ ለይቶ ማየት ነው። ኃይሌ ፊዳ፣ ብርሃነ መስቀል ረዳና ሠናዬ ልኬ፣ ወዘተ ቢስማሙ ኖሮ የአብዮት እሳት የኢትዮጵያን ልጆች በልቶ የተረፉትን በስደት ምድር ባልተፋ። ለማፍረስና ለማስተባበር የመሪዎች ሚና እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም። ሦስቱም ከነአንጃዎቻቸው ለራሳቸው እንጂ የማያጋሩትን የሥልጣን ወንበር ፈለጉ፤ እንኳን ሥልጣን ሕይወታቸውንም አጡ። ሲቀራቀሱ በከፈቱት ቀዳዳ የደርግ፣ የሶቭየት ሕብረትና የምሥራቅ ጀርመን ጅቦች ገብተው ምድሪቱ ላይ ተሳረሩ። የታሪክ አምላክ ካለፈው እንማር እንደ ሆነ ወይም ስንፍናችንን እንደግም እንደ ሆነ ሊፈትነን የማይደገም ሌላ ዕድል አቅርቦልናል። ያመልጠን ይሆን? በተረፈ ኢሕአፓ፣ ደርግና መኢሶን የሠላሳ አምስት ዓመት ቁርሾአቸውን ሊፋለሙ ማንዣበብ ትተው ዘመንና ትውልድ ጥያቄው እንደ ተለወጠ ማሰብ ይበጃቸዋል።

ዛሬ ግን አንድ የተለየ ተስፋ ቢኖር የሕዝቡ ንቃት ካለፈው የላቀ መሆኑ ነው። ቢስማማ ግራ የሚያጋቡትን መሪዎቹን ሊፈነግል እንደሚችል መረዳቱ ነው። ፈጽሞ አይወናበድም ማለት ግን አይቻልም። ከሚያወናብዱት ለማዳን መድኃኒቱ ሕዝቡ ያመነባቸው መሪዎቹ መስማማትና አቋማቸውን በየወቅቱ ደጋግመው ግልጽ ማድረግና ማሰማት ነው። ከመስማማት ደግሞ አልፈው በዙሪያቸው ለአማካሪነት የሰበሰቧቸውን ማንነት፣ ታማኝነትና ችሎታ ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል። በቀጥታ እምነት ለጣለባቸው ሕዝብ ያለ አስተርጓሚና ያለ አማላጅ እቅዳቸውን ማስታወቅ ይጠበቅባቸዋል። በዝምታ ማለፍ ሳይሆን ለማወናበድ የማይተኙ እንዳሉ አውቆ ምላሹን እጅበጅ መስጠት ያሻቸዋል።

ምዕራባውያንን ማስረዳት የሚችሉ በባሕሉ፣ በቋንቋውና በጥበቡ የተካኑትን እንደ ፕሮፌሰር አለማየሁ ያሉትን ፈልጎ ማስጠጋት ያስፈልጋል። የነዚህ ግለሰቦች ተሳትፎ ያስገኘውን ለውጥ አሁን እንኳ ማየት ተችሏል። ለዚህም ነው ፕሮፌሰር አለማየሁና አባሮቹ የኢትዮጵያን ጎልውና ለማፍረስ ታጥቀው የተነሱ ናቸው ብሎ የሚናፈሰውን አሉባልታ ማመን የሚያዳግተው። ለሚነዛው ወሬ ሺህ መልስ ለመስጠት ከመሯሯጥ ቀድሞ መዘጋጀትና ለከፊሉ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የሚተርፍ ተስፋና ራእይ ማብሰር ይበጃል።

ሌላኛው የቅንጅት ስም ለውጥ ጉዳይ ነው። ቅንጅት ሕጋዊ ሰውነት እንዲኖረው ስሙን መቀየር ይኖርበታል ተብለናል። መጠሪያ ብቻ ሳይሆን ስም ጎልውናና ዓላማን አመልካች ነው። በውስጡ

ያቀፈውን ማህበርተኛ የማያያዝና የማጎልበት ሥራ ይኖረዋል። የድርጅታችሁን ስም ካልለወጣችሁ ፈቃድ አልሰጥም ማለቱ የኢሕአዴግን ስልት የበላይነት በግልጽ ያሳያል። የቅንጅትን አመራር የሚያማክሩ ምን ዓይነት ልምድ እንዳላቸው ማወቅ ባንችልም በተደጋጋሚ የሚታየው ለዴሞክራሲያዊ አሠራርና ልምድ ብዙ እንደሚቀራቸው ነው። ኃላፊነትን ለመጋራት ካለመፍቀድ የተነሳ ይሆን? ከክልላቸው ወጣ ያለውን ከአለመተማመን የተነሳ በማግለላቸው ይሆን? ሰሞኑን የታየው የገንዘብ መዋጮ እንደዚህ ላለ ዋነኛ ጉዳይ ሊውል ይገባል እንላለን።

ለማንኛውም የስም ለውጥ እንደ ትልቅ ጉድ ሊታይና ግርግር ሊያስነሳ አይገባም። ስሙን ወረቀት ላይ ማስቀረት ይቻላል። በሌላ አነጋገር ሕዝቡ የቀደመውን ስም እንዳይጠቀም የሚከለክለው ኃይል የለም። ደርግ መስቀል አደባባይን "አብዮት አደባባይ" ብሎ እንደ ሰየመው ዘመን ማለት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ያንኑ ሃይማኖቱን ይዞ "መስቀል፣ መስቀል" እንዳለ ዘመን ተለውጦ እንደገና "መስቀል" ይዞ አደባባይ ሊወጣ ችሏል። መንግሥት ጊዜያዊ ነው፤ ሕዝብ ግን የሚሰነብት ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው።

የሰላምና ደህንነት አስመጪና ላኪ

ሁለት ዓመት ብዙ አሳየን። ዛሬ ወሬው "ሰላምና ደህንነት፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነጻነት" ሆኗል። ሰብአዊ መብት ደግሞ ከውጭ መንግሥታት እርዳታ ጋር ተያይዟል። "ሰብአዊ መብት አስከብር አለዚያ እርዳታ ታጣለህ" ነው። ከአስራ አምስት ዓመት በፊት ይኸ ሕግ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ ይኸ መንግሥት ባልጸና። ዘመን ይለዋወጣል። አያስተማምንም። ይልቅ የሚበጀው ይህንን መገንዘብና መቻቻሉ ነው፤ የአገርን ጥቅምና ክብር ለማስጠበቅ መጣሩ ነው። ይኸ መንግሥት "ዲ ኤል ፓይፐር" ለተሰኘ ውቃቢ በየወሩ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር እየገበረ ፈቃዱን ያስፈጽማል። ሃምሳ ሺህ ዶላር ማለት በቀን አንድ ዶላር (ዘጠኝ ብር) ሂሳብ ለሃምሳ ሺህ ኢትዮጵያዊ የዕለት ጉርስ በቀቶ የሚተርፍ ወጪ ማለት ነው። ፓይፐር ምን ገዶት? ባልወለደ አንጀቱ ከደሃ ኢትዮጵያዊ አፍ እየነጠቀ ይንደላቀቃል። የራሱ መንግሥትና ወገን ካልገደደው እኔ ምን ገዶኝ ምላሹ ነው።

ሌላው ወገን ደግሞ ዶናልድ ፔይንና ክሪስ እስሚዝ የተሰኙ የአሜሪካ የሕዝብ መማክርትን ሙጢኝ ብለዋል። የመንግሥትን በደል ለማስቀምና ለመቀልበስ ይህ ዓይነቱ አድራጎት ተገቢነቱ ባይካድም የሚታየው እንቅስቃሴ አንድ ላይ ሲታይ ጉስቁልናችንንና አመጸኛነታችንን አጉልቶ ያሳያል። ማስተዋል ይስጥ።

ይኸ ሳያንስ ሌላ ጉድ ደግሞ ተከስቷል። ይኸውም "በኢትዮጵያ ሰላምንና ደህንነትን ለማዳበር፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነጻነትን እንዲስፍኑ ለማበረታታትና የወጣ ሕገ-ረቂቅ 2003" ደጋፊና ተቃዋሚ ማፍራቱ ነው። ሕገ ረቂቁን መንግሥት አልደገፈውም። ከመንግሥት ጋር ያበሩ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያውንም እንደዚሁ ተቃውሞ እያሰሙ ነው። ተቃውሞው የአገራችንን ነልውናና ሉዑላዊነት ይጻረራል ነው። እንዲያውም ቅኝ ተገዝተን የማናውቀውን ነጻነታችንን ለባዕድ መንግሥት አሳልፎ ይሰጣል ነው። ከነዚሁ ወገኖቻችን ይህ አሳብ መምጣቱ በጣሙን አስቂኝ ድራማ አስመስሎታል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ኤርትራ፣ ስለ አሰብ፣ ጎንደር አካባቢ ስላለው መሬት ውይይት አለመደረጉ መች ተረሳውና ነው?

በህወኃት መካከል የደረሰው መሰንጠቅ ለዓለም ባንክ እርዳታ መንበርከክ የአገር ነልውናን ከመሸጥ አይለይም ሰንባል አልነበረምና ነው? ደግሞስ ነልውናችንን የሚጻረር ከሆነ የውጭ እርዳታ ላለመቀበል መብቱ እኮ የኛ ነው። የምንቀበል ከሆነ ደግሞ ገንዘባችሁን ላኩልን ምን

ላይ እንዳዋልነው ግን አትጠይቁን ማለት የሌባ ዓይነ ደረቅ አያሰኘንም ወይ? ባጭሩ፣ ክብራችንን የምንጥልና የምናነሳ እኛው ነን። ክቡር ዶናልድ ፔይንና አጋራቸው እንደ ሆኑ ሙግታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ መስሎን ብዙ ስግደት ከመስጠት እንቆጠብ። ሁለቱ መማክርት በመጀመሪያ አሜሪካዊያን ናቸው፤ በሁለተኛም ደረጃ ያው አሜሪካውያን፣ የአገራቸውን የአሜሪካንን ጥቅምና የመረጣቸውን ክፍል መብት ጠባቂዎች ናቸው። የኛ ጉዳይ እግረ መንገድ የተገኘ ነው። በተጨማሪ የአሜሪካን ኢትዮጵያውያን ትግል ውጤት ነው። ትግሉ ሲቀዘቅዝ፣ የአሜሪካን ጥቅም አንሶ ሲገኝ እርግፍ ተደርጎ የሚቀር ነው። እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 2001 ሽብር ፈጣሪዎች አደጋ ባይጥሉ ኖሮ አሜሪካኖች የት እንዳለንም አያስቡም ነበር። እና አንታለል፤ ልባችንን በብዙ አንጣልበት።

"በኢትዮጵያ ሰላምንና ደህንነትን ለማዳበር፣ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ዴሞክራሲና የኢኮኖሚ ነጻነትን እንዲሰፍኑ ለማበረታታትና ለማመቻቸት የወጣ ሕገ-ረቂቅ 2003" ደግሞ ሌላም ጎን አለው። ይኸውም ሰብአዊ መብት የጣሱ እንደ አቶ ቀልቤሳ ያሉ ግለሰቦች ባሕር ማዶ ሸሽተው እንዳይደበቁ፣ የባንክ ሂሳብና ንብረት እንዳያንቀሳቅሱ የሚያግድ ነው። በተረፈ ሕጉ ረቀቀ ማለት በአልኸኞች ምድር በቀላሉ ተፈጻሚነትን ያገኛል ማለት እንዳይደለ መገንዘብም ይበጃል።

ሰሞኑን ደግሞ የ"ፖለቲካና የሃይማኖት ጥናት ኢንስቲትዩት" የተሰኘ "ሕገ-ረቂቅ 2003" የአሜሪካን ደህንነት ከአደጋ ላይ የሚጥል ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ የተጀመረውን የዴሞክራሲ ሂደት የሚያደናቅፍ ነው ብሎ መግለጫ ብጤ አውጥቷል። ይኸ ድርጅት በኢትዮጵያ ጉዳይ ከዚህ ቀደም አለመሳተፉ ከበስተኋላ ሌላ እጅ ለመኖሩ አንድ ማስረጃ ነው። ዓላማው ሕገ-ረቂቁ በመወሰኛው ምክር ቤት እንዳይጸድቅ ለማጨናገፍ ነው። ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅም የዚሁ ኢንስቲትዩት የቦርድ አባል መሆናቸው ኢሕአዴግንና የታሰሩ የቅንጅት መሪዎችን ለማስማማት ባደረጉት ጥረት ላይ ምን ትርጉም እንደሚጨምር በውል ማወቅ ያዳግታል። የተጠቃሹ ድርጅት ቦርድ እንደዚሁ ከሳውዘርን ባፕቲስት መሪዎች አንዱና የፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ አማካሪ የሆኑትን ሪቻርድ ላንድንም ይጨምራል።

የጠ/ሚኒስትር መለስ መንግሥት ሰብአዊ መብት የሚያከብር ከሆነ፣ የዜጎችን የመምረጥ፣ የመጠየቅና ተመራጩን የማሰናበት መብትና የሕግ የበላይነትን የሚያስከብር ከሆነ፣ የሚቀበለውንም እርዳታ በውሉ ሥራ ላይ የሚያውል ከሆነ ምን ያሳሰበዋል? እርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ መብት ለዜጋው መለቀቁ የሚያስፈራቸው አይታጡም። ዴሞክራሲ የያንዳንዱን የሕብረተሰብ ክፍል መሳተፍ ይጠይቃልና። በዚሁ ሥርዓት መሠረት ንኡስ መሆን አያስጠቃም። ንኡሳን ጎሣዎችም ጥቅማቸውን ለማስከበር ቢሹ ለብቻቸው ከመቆም ይልቅ ከሌሎች ዓላማቸውን ከሚጋሩ ጋር መደመር እንደሚኖርባቸው ያስረዳል። አለበለዚያ ድምጻቸው ይታቀባል፤ ጥቅማቸው ይጓደላል።

*ሥርአተ አልበኛና የሚመጣው መንግሥት*

ትርምስ መፈጠሩ ለማንም አይበጅም። የመንግሥትና የቅንጅት ዛቻ ትርፉ አለመተማመንን ከመፍጠር አልፎ ለበጎ ዓላማ ሊውል የሚገባን የአገር ሀብት በየሜዳው መዝራት ሆኗል። ትርምስ ለሌባ ያመቻል፤ ወደ ሥርአተ አልበኛነት ያመራል። ከሥርአተ አልበኛነት ደግሞ የኢሕአዴግ መኖር ይመረጣል። ልብ እንበል፦ የኢሕአዴግ መንግሥት ይመረጣል አላልኩም። ሥርአተ አልበኛነት ከሚነግሥ መጥፎ የተባለው የኢሕአዴግ መንግሥት ይመረጣል ነው ያልኩት። የቀይና ነጭ ሽብር ዘመን ይታሰበን። ኮሎኔል መንግሥቱ አገር ጥለው ሲወጡ የነበረው ጭውታ ይታሰበን። ያን ሁኔታ መድገም መከራችንን ማራዘም ይሆናል።

ሌላኛው ጉዳይ የለውጥ አስፈላጊነት ነው። የቅንጅት መሪዎች ሥልጣን ሲይዙ ዛሬ በሥልጣን ላይ ባሉት ላይ የምንጠላውን ገጸ ባሕርይ አናይባቸውም ማለት አንችልም። እነዚህም ሥልጣናቸውን ላለመልቀቅ ይከፋፍሉን ይሆን? የገቡትን ቃል በየወንዙ ይለዋውጡ ይሆን? በሥልጣን ላይ የመቆያ ዘመን ይወስኑ ይሆን? ጦር ሜዳ ያግ-ዙን ይሆን? ያለ ፍትሕ ከርሼሌ ያወርዱን ይሆን? የመናገር መብታችንን በሰንካላ ምክንያት አሳብበው ይነጥቁን ይሆን? ብቃት የሌላቸውን ዘመዶቻቸውን ኃላፊነት ላይ ይመድቡ ይሆን? ውጭ አገር ባንክ ሂሳብ ከፍተው አገሪቷን ያራቁቱ ይሆን? ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን ውጭ አገር እያስተማሩና እያሳከሙ ስለ አገሪቱ ትምህርትና ጤና እድገት አይገዳቸው ይሆን? እርግጠኛ መሆን አንችልም። ከሰው የተለዩ አይደሉምና። እኛም እኰ ሰዎች ነን። ከዛሬ ነገ ይሻላል ብለን በተስፋ እንኖራለን። ቢሆንም የመቀባበልና የመሪነት ባሕል እንዲዳብር ሌሎች መሞከራቸው ተገቢ ነው። ሕዝቡም ዴሞክራሲ የሚሉትን ጉሽ ቀምሷልና፣ ተሳክሯል፤ ከንግዲህ በዋዛ አይበገርም።

በየመስኩ ችሎታ ያካበቱ ሥነ ምግባርና ርኅራኄ ያለባቸው አእምሮአቸውና ልባቸው ሰፊ የሆነ ዕድል ይሰጣቸው። ያም ማለት አሁን ያለው ሁሉ ተጠራርጎ እንደገና አዲስ ሥርአት አዲስ ጅምር ይምጣ ማለት አይደለም። ቀድሞውንም የችግራችን መንስዔ በጅምላ ማውገዝ ነውና፤ ሳንገነባ ማውደም ነውና። አሁንም እንኳ የቅንጅት መሪዎችን መወንጀል ተይዟል። ዶክተር ብርሃኑ የአገሪቱን ጥቅም ሸጧል እየተባለለት ነው። ወ/ት ብርቱካን ልምድ ይጎድላታል። ሌሎችም እንደዚሁ ሌላ ሌላ። መተቸት ያለ ነገር ነው። በአንጻሩ ራሳቸውን ሊሾሙ ለሚሹ ማንም ምንም እንደማይጥማቸው መገንዘብ ይቻላል። ግርግር መፍጠር እንጂ ቁም ነገር አይሰማባቸውም። ስለ ችሎታ ከታሰበ ግን አሁን የምናያቸው የቅንጅት መሪዎች የዛሬ 17 ዓመት ከታዩት የህወኃት መሪዎች እጅጉን ቢበልጡ እንጂ እንደማያንሱ ምስክር መጥራት አያሻም።

በተረፈ፣ በዚህ መንግሥት የተጀመሩ ውጥኖችና ተግባራዊ እየተደረጉም ያሉትን ለይቶ ማጽናት ያሻል ማለት ነው። ሥር-ነቀልና አዲስ ጅማሬ አመጣለሁ የሚለንን ግለሰብ ሆነ ድርጅት በጥርጣሬና በዓይነ ቁራኛ ማየት ይኖርብናል።

*መደምደሚያ*

አሁን ላሉት መሪዎች ጥያቄ ማቅረብ ቢቻል እነሆ፦ በእስር የማቀቁት ወራት እንደ ቀላል ባይታይም፣ ክቡር ኢንጅኔር ኃይሉ ሻውል መሪነታቸውን ዛሬውኑ መልቀቃቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከብዙ አሣር የሚያድን ሆኖ ቢገኝ ይህን እንኳ እርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኛ ናቸው? ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ ያላቸው ፍቅር እስከ ምን ድረስ ነው? ወይስ ያለ እርሳቸው ተሳትፎ አገር የምትጠፋ መስሎ ይታያቸዋል? ይኽ ጥያቄ መሪ ነኝ ለሚል ሁሉ ነው። የታሪክ ክብር ክብራቸውን ለጋራ ጥቅም ለሚሠው ነው። ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለክቡር ሀዲስ አለማየሁ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ሲያቀርብላቸው ይቅርብኝ ማለታቸው ክብራቸው ሆኖ ይኖራል።

አንዳንዴም እኰ መሪነት የጋራ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ ለሌሎች ተራ መልቀቅንና ለአገራዊ ኃላፊነት ማብቃትን ይጨምራል። ያሉት መሪዎች መስማማት ካልቻሉ ደግሞ ነገር ሁሉ እንደ ተበላሸ ሊቆጠር አይገባም። አምባገነንነት አያንሰራራ እንጂ አንዱ ለሌላውና ለሕዝቡ ተጠሪ እስከሆነ ድረስ የሕግ የበላይነት እስከ ተጠበቀ ድረስ የዴሞክራሲ ሥርዓት የማይፈታው ችግር አይኖርምና።

Copyright October 14, 2007 by Mitiku Adisu
All rights reserved